# ልሳነ ግእዝ

## አንደኛ ክፍል



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን  የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ዓለም አቀፍ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ

## መግቢያ (ሙባዕ)

ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ቋንቋዎች ባለቤት ስትኾን የግእዝ ቋንቋ ከቀደምት ቋንቋዎች ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል። የግእዝ ቋንቋ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ ሆኖ ለረጅም ዘመናት ያገለገለ ሲኾን ለሀገራችን የሥነ ጽሑፍ እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል። በመሆኑም አያሌ ቅዱሳት መጻሕፍት የጥበብ መጻሕፍት የታሪክ መዛግብት እንዲሁም ጥንታውያን ቅኔያት የተጻፉት በግእዝ ቋንቋ በመኾኑ ቤተ ክርስቲያናችንን ፤ሀገራችን ኢትዮጵያን እንዲኹም የአባቶቻችንን ጥንታውያን ጥበቦች ለመረዳት የግእዝን ቋንቋ ማወቅ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው።

አባቶቻችን ልጆቻቸውን በመንፈሳዊ ዕውቀት እና ሥነ ምግባር በማነጽ ለቤተክርስቲያን እና ለሀገራችን ተተኪ ትውልድን እያፈሩ እዚህ ካለንበት ዘመን ደርሰናል። ከነዚኽም የማስተማር ጥበባት አንዱ የቃል ትምህርት ሲኾን ይህ ትምህርት ልጆች የጸሎት መጻሕፍትን በቃል እየተነገራቸው እነርሱም ደጋግመው በመናገር ቃላቱን እንዲይዙ እና ጸሎታቸውን በቃላቸው ማድረስ እንዲችሉ የሚያደርግ ነው። ስለሆነም ይህ ትምህርት ከአባቶቻችን የወረስነውን የማስተማር ጥበብ በመከተል ቤተክርስቲያንን የሚረከቡ ካህናትን እና ምእመናን ለማፍራት ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

# መክስተ ርዕስ (ይዘት)

## አርእስት

መግቢያ

የትምህርቱ ዓላማ

ምዕራፍ አንድ

ከአዳም እስከ ኖኅ ያሉ የአበው ታሪክ

፩. ፩ ሥነ ፍጥረት

፩. ፪ አዳም እና ሔዋን በኤደን ገነት

፩. ፫ የአቤልና የቃየን ታሪክ

፩. ፬ የኖኅ ታሪክ

፩ ፭ የባቢሎን ግንብ

ምዕራፍ ሁለት ........

ከአብርሃም እስከ ሙሴ

፪. ፩ የአባታችን የአብርሃም እና የሣራ ታሪክ

፪. ፪ የይስሐቅ ልደትና እድገት

፪. ፫ የያዕቆብ እና የኤሳው ታሪክ ......

፪. ፬ የያዕቆብ ልጆች ታሪክ..........

፪ ፭ የራሔል ታሪክ

፪. ፮ የያዕቆብ ልጅ የዮሴፍ ታሪክ

፪. ፯ የሙሴ መወለድና እድገት

፪. ፰ ለእስራኤላዊያን መና ከደመና መውረዱና ውኃ ከዓለት መፍለቁ

፪. ፱ የሙሴ እኅት ማርያም

ምዕራፍ ሦስት ...

ከኢያሱ እስከ ዳዊት..........

፫.፩. የኢያሱ ታሪክ

፫.፪. የሶምሶን ታሪክ

፫. የጌዴዎን ታሪክ

፫.፬. የሩት እና የኑኃሚን ታሪክ

፫፭ የሳሙኤል እናት የሐና ታሪክ

## የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው እንደጨረሱ ፦

፩ የፊደላትን ቅርጽ እና ድምፅ በሚገባ ይለያሉ።

፪ እስከ መቶ ያሉ የግእዝ ቊጥሮችን በሚገባ ይለያሉ።

፫ መልእክተ ዮሐንስን በአራቱም የንባብ አይነት( በቊጥር፣ በማጋዝ፣ በውርድ፣ በቊም ንባብ) ይይዛሉ።

፬ የግእዝ ቊጥሮችን ጠንቅቀው አውቀው በተጠየቁ ጊዜ ይመልሳሉ መጽሐፍ ቅዱስን ያለምንም የቁጥር ስህተት ማንበብ ይችላሉ።

፭ የስልክ ቁጥር እና የቤት ቊጥርን በግእዝ ይጽፋሉ።

፮ በቃላቸው ከአአትብ ገጽየ ጀምረው እስከ በሰላመ ገብርኤል ድረስ በየቀኑ ያደርሳሉ።

፯ መርሐ ግብራቸውን በግእዝ ጸሎት ይከፍታሉ ይዘጋሉ።

፰ ዐሥሩን መራሕያን ይለያሉ በተጠየቊም ጊዜ ይመለሳሉ።

፱ የቤተሰብ ስም ዝርዝር ይለያሉ።

# ምዕራፍ አሐዱ
# ፊደል

## የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የግእዝ ፊደላትን እና የአቡጊዳ ተረፎችን በሚገባ ያውቃሉ ይለያሉ፤
- ከአአትብ ገጽየ እስከ በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል ድረስ በቃላቸው ይይዛሉ፤
- መልእክተ ዮሐንስን በአራቱም የንባብ አይነት(በቍጥር፣በማጋዝ በውርድ፣በቊም ንባብ) ይይዛሉ፤

## ተስእሎታተ መራኁት (የመክፈቻ ጥያቄዎች)

፩. አርድእት ዘይተልዉ ፊደላተ አንብቡ ለመምህርክሙ (ተማሪዎች የሚከተሉትን ፊደላት ለመምህራችሁ አንብቡላቸው)።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ው | ዉ | ዪ | ይ | ፉ |
| ፋ | ዋ | ዎ | | |

፪. አርድእት እስኩ በሉ አቡነ ዘበሰማያት ለመምህርክሙ (ተማሪዎች አቡነ ዘበሰማያትን ለመምህራችኹ በሉላቸው)?

፫. (እምቅድመ ዝ መዋዕል ማእዜ ማእዜ ትብልዎ ለዝንቱ ጸሎት) ከዚህ ቀደም ይህንን ጸሎት መቼ፣መቼ እንደምትጠቀሙት ለመምህራችሁ ንገሩ።

## ፩. ፊደል

**ፊደል፦** ማለት ፈደለ፤ ጻፈ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲኾን ትርጉሙም የጽሕፈት ኹሉ መጀመሪያ፣ ምልክት፣ የመጽሐፍ ሁሉ መነሻ ማለት ነው። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌም ሲተረጉሙት በቁሙ "ልዩ፣ ምርጥ ዘር፣ ቀለም፣ ምልክት፣ አምሳል፣ የድምፅና የቃል መልክ ሥዕል፣ መግለጫ፣ ማስታወቂያ ማለት ነው።" ይላሉ።

## ፩.፩ የግእዝ ፊደል ቀዳማውያን አበገደ ፊደል ማጋዝ

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ቡ | ጊ | ዳ | ሄ | ው | ዞ |
| በ | ጉ | ዲ | ሃ | ዌ | ዝ | ሖ |
| ገ | ዱ | ሂ | ዋ | ዜ | ሕ | ጦ |
| ደ | ሁ | ዊ | ዛ | ሔ | ጥ | ዮ |
| ሀ | ዉ | ዚ | ሓ | ጤ | ይ | ኮ |
| ወ | ዙ | ሒ | ጠ | ዬ | ክ | ሎ |
| ዘ | ሑ | ጢ | ያ | ኬ | ል | ሞ |
| ሐ | ጡ | ዪ | ካ | ሌ | ም | ኖ |
| ጠ | ዩ | ኪ | ላ | ሜ | ን | ሦ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የ | ኩ | ሲ | ማ | ኔ | ም | ያ |
| ከ | ሉ | ሚ | ና | ሜ | ዕ | ፎ |
| ለ | ሙ | ኒ | ሣ | ዔ | ፍ | ጸ |
| መ | ኑ | ሢ | ዓ | ፌ | ጽ | ቆ |
| ነ | ሡ | ዒ | ፋ | ጼ | ቅ | ሮ |
| ሠ | ዑ | ፊ | ጻ | ቄ | ር | ሶ |
| ዐ | ፉ | ጺ | ቃ | ሬ | ስ | ቶ |
| ፈ | ጹ | ቂ | ራ | ሴ | ት | ኖ |
| ጸ | ቁ | ሪ | ሳ | ቴ | ኅ | ፆ |
| ቀ | ሩ | ሲ | ታ | ኄ | ፅ | ጾ |
| ረ | ሱ | ቲ | ኃ | ፄ | ጽ | ፖ |
| ሰ | ቱ | ኂ | ፃ | ጼ | ፕ | ኦ |
| ተ | ኁ | ፂ | ጳ | ፔ | እ | ቦ |
| ኀ | ፁ | ጲ | ፓ | ኤ | ብ | ኆ |
| ፀ | ጱ | ፒ | ኣ | ቤ | ግ | ጸ |
| ጰ | ፑ | ኢ | ባ | ጌ | ጽ | ሆ |
| ፐ | ኡ | ቢ | ጋ | ጼ | ህ | ዎ |

ድምር ፳፮ (26)

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀ | ቈ | ቍ | ቊ | ቌ | ቍ |
| ኀ | ኈ | ኍ | ኊ | ኌ | ኍ |
| ከ | ኰ | ኵ | ኲ | ኴ | ኵ |
| ገ | ጐ | ጕ | ጒ | ጔ | ጕ |

ምልማድ አሐዱ

፩. ጸሐፉ ዘይተልዉ ፊደላት ዳግመ (የሚከተሉትን ፊደላት አስመስላችኹ በድጋሚ ጻፉ)

፩ ደ _______ _______ _______ _______ _______ _______ _______

፪. ኀ _______ _______ _______ _______ _______ _______ _______

፫. ፀ _______ _______ _______ _______ _______ _______ _______

፬. ጸ _______ _______ _______ _______ _______ _______ _______

፭. ፐ _______ _______ _______ _______ _______ _______ _______

፪. የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች የሚጎድለውን ፊደል በመለየት ሙሉ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | ቀ | | ቍ | | ቋ | ቍ |
| ፪ | ኀ | ኈ | | ኊ | | ኍ |
| ፫ | ከ | ኰ | | ኲ | ኴ | ኵ |
| ፬ | ገ | ጐ | ጕ | | ጔ | |

## ፪ ከግእዝ ፊደላት የተደቀሉ የዐማርኛ ፊደላት

| የግእዝ ፊደላት | የዐማርኛ ፊደላት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ደ | ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ዘ | ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| ጠ | ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ከ | ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ነ | ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| ሰ | ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ተ | ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |

## ፩፥፫ ጉባኤ ዝርዋን ፊደላት

### ፩፥፫፥፩ ፊደላተ ግእዝ ወዐምሐራ (የዐማርኛ እና የግእዝ ፊደላት)

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ተ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |

**አማ(**

| ግእዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ሐምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |

| ግእዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ሐምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |

## ምልማድ ክልኤቱ

፩. (ምልዑ ርቱዐ አውሥዖተ በውስተ መካነ በድው) በባዶው ቦታ የጎደሉትን ፊደላት ሙሉ።

ሀ. ሀ _____ ሂ ሃ _____ ህ ሆ

ለ. ለ ሉ _____ ላ ሌ ል _____

ገ. _____ _____ ሚ ማ ሜ _____ ሞ

፪. አውሥኡ ዘይተልዉ ጥያቄያት (የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትእዛዙ መሠረት መልሱ)።

ሀ. በምንት ይትሌለዩ "ሀ" ወ "በ" ፊደላት ("ሀ" እና "በ" የሚለያዩት በምን ነው?)

ለ. "ጠ" ወ "ሠ" ዘይሰመዩ ፊደላት አሐዱ እሙንቱ ለእመ ኢኮኑ አሐደ በምንት ይትሌለዩ ("ጠ" እና "ሠ" አንድ አይነት ናቸው? ካልሆኑ በምን ይለያያሉ?)

ገ. ይትሌለዩኑ "ኀ" ወ "ነ" ፊደላት ለእመ ሀሎ ለያልይ በምንት ይትሌለዩ ("ኀ" እና "ነ" ይለያያሉ? ከተተለያዩ እንዴት?)

፫. ዘይተልዉ ፊደላተ አንብቡ በቃልክሙ ወጸሐፉ በጽሑፍ (የሚከተሉትን ፊደላት በቃላችሁ ደጋግማችሁ ጥሯቸው ደጋግማችሁም ጻፏቸው)

ሀ. "ው" እና "ዉ"

ለ. "ዩ" እና "ይ"

ገ. "ፉ" እና "ፋ"

ደ. "ዋ" እና "ዎ"

ሀ. "ወ" እና "ዎ"

## ፩፥፬ የቃል ጥናት

### ፩፥፬፥፩ አአትብ ገጽየ፣ ነአኲተከ ንባብ እና የቃል ጥናት

አአትብ ገጽየ ወኵለንታየ በትእምርተ መስቀል

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

በቅድስት ሥላሴ እንዘ አአምን ወእትመኀፀን

እክሕደከ ሰይጣን በቅድመ ዛቲ እምየ ቅድስት ቤተክስቲያን

እንተ ይእቲ ስምዕየ ማርያም ጽዮን ለዓለመ ዓለም።

ነአኵተከ እግዚኦ ወንሴብሐከ ንባርከከ እግዚኦ ወንትአመነከ
ንገኒ ለከ እግዚኦ ወንትቀነይ ለስምከ ቅዱስ ንሰግድ ለከ ኦ፣ ዘለከ
ይሰግድ ኵሉ ብርክ ወለከ ይትቀነይ ኵሉ ልሳን
አንተ ውእቱ አምላከ አማልክት ወእግዚአ አጋዕዝት
ወንጉሠ ነገሥት አምላክ አንተ ለኵሉ ዘሥጋ
ወለኵሉ ዘነፍስ ወንጼውዐከ በከመ መሀረነ
ቅዱስ ወልድከ እንዘ ይብል አንትሙሰ ሶበ ትጼልዩ ከመዝ በሉ።

**፩፥፬፥፪ አቡነ ዘበሰማያት ወ ሰላም ለኪ ንባብ እና የቃል ጥናት**

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ ትምጻእ መንግሥትከ ወይኩን
ፈቃድከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር ሲሳየነ
ዘለለ ዕለትነ ሀበነ ዮም ኅድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ
ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ። ኢታብአነ እግዚኦ
ውስተ መንሱት። አላ አድኅነነ ወባልሐነ እምኵሉ እኩይ
እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም።
በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ
ኦ እግዝእትየ ማርያም ሰላም ለኪ
ድንግል በኅሊናኪ ወድንግል በሥጋኪ
እመ እግዚአብሔር ጸባዖት ሰላም ለኪ
ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ
ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ
ሰአሊ ወጸልዩ ምሕረተ ኀበ ፍቁር ወልድኪ ኢየሱስ ክርስቶስ
ከመ ይስረይ ለነ ኃጣውኢነ።

## ምልማድ ሠለስቱ

፩. ከዚህ በታች ያለውን ንባብ በማንበብ የጎደሉትን ቃላት ወይም ዐረፍተ ነገር ሙሉ።

አአትብ ገጽየ__________________ በትእምርተ መስቀል በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
አሐዱ አምላክ በቅድስት ሥላሴ እንዘ አአምን __________________ እክህደከ ሰይጣን በቅድመ
ዛቲ ____________________________ እንተ ይእቲ ስምዕየ ማርያም ጽዮን ለዓለመ ዓለም።

፪. ነአኵተከ እግዚኦ ________________ ንባርከከ እግዚኦ ወንትአመነከ ንስእለከ እግዚኦ ________________ ንገኒ ለከ እግዚኦ ወንትቀነይ ለስምከ ቅዱስ ንሰግድ ለከ ኦ ዘለከ ይሰግድ ኵሉ ብርክ ወለከ ________________ ኵሉ ልሳን አንተ ውእቱ ________________ ወእግዚአ አጋዕዝት ወንጉሠ ነገሥት ________________ ለኵሉ ዘሥጋ ወለኵሉ ዘነፍስ ወንጼውዐከ በከመ መሐረነ ቅዱስ ወልድከ እንዘ ይብል አንትሙሰ ሶበ ትጼልዩ ከመዝ በሉ

## ፩፥፫ የግእዝ ንባብ

ተማሪዎች ከዚኽ በታች ያለውን መልእክተ ዮሐንስ በቍጥር፣ በማጋዝ፣ በውርድ እና በቁም ንባብ ያንብቡ። መምህር/ት እባከዎን በአራቱም ንባብ ያስነብቧቸው።

### ፩፥፫፥፩ መልእክተ ዮሐንስ በቍጥር፣በማጋዝ

መ ል እ ክ ተ፡ ዮ ሐ ን ስ፡ ሐ ዋ ር ያ፡ ወ ል ደ፡ ዘ ብ ዴ ዎ
ስ፡ ቀ ዳ ማ ዊ፡ ን ዜ ን ወ ክ ሙ፡ በ እ ን ተ፡ ው እ ቱ፡ ዘ ሀ
ሎ፡ እ ም ቅ ድ ም፡ ው እ ቱ፡ ዘ ሰ ማ ና ሁ፡ በ እ ዘ ኒ ነ፡ ወ
ዘ ር ኢ ና ሁ፡ በ አ ዕ ይ ን ቲ ነ፡ ወ ዘ ጠ የ ቅ ና ሁ፡ ወ ዘ
ገ ሠ ሣ ሁ፡ እ ደ ዊ ነ፡ በ እ ን ተ፡ ነ ገ ረ፡ ሕ ይ ወ ት። እ ስ
መ፡ ሕ ይ ወ ት፡ ተ ዐ ው ቀ ት፡ ለ ነ፡ ወ ር ኢ ና ሃ፡ ወ ስ ማ
ዐ፡ ኮ ነ፡ ወ ን ዜ ን ወ ክ ሙ፡ ለ ክ ሙ ኒ፡ ሕ ይ ወ ተ፡ እ ን
ተ፡ ለ ዓ ለ ም፡ እ ን ተ፡ ሀ ለ ወ ት፡ ኀ በ፡ አ ብ፡ ወ ተ ዐ ው
ቀ ት ለ ነ። ወ ር ኢ ና ሃ፡ ወ ሰ ማ ዕ ና ሃ፡ ወ ን ዜ ን ወ ክ
ሙ፡ ለ ክ ሙ ኒ፡ ከ መ፡ አ ን ት ሙ ኒ፡ ት ኩ ኑ፡ ሱ ታ ፌ፡
ም ስ ሌ ነ፡ ወ ሱ ታ ፌ ነ ሰ፡ ም ስ ለ፡ አ ብ፡ ወ ም ስ ለ፡ ወ
ል ዱ፡ ኢ የ ሱ ስ፡ ክ ር ስ ቶ ስ። ወ ዘ ን ተ፡ ን ጽ ሕ ፍ፡ ለ
ክ ሙ፡ ከ መ፡ ት ፍ ሥ ሕ ት ክ ሙ፡ ፍ ጽ ም ተ፡ ት ኵ ን፡
ብ ነ። ወ ዛ ቲ፡ ይ እ ቲ፡ ዜ ና፡ እ ን ተ፡ ሰ ማ ዕ ና ሃ፡ ት ካ
ት፡ እ ም ኔ ሁ፡ ወ ን ዜ ን ወ ክ ሙ፡ ከ መ፡ እ ግ ዚ አ ብ
ሔ ር፡ ብ ር ሃ ን፡ ው እ ቱ፡ ወ ጽ ል መ ት ሰ፡ አ ል ቦ፡ ኀ ቤ

ሁ፡ ወ ኢ አ ሐ ተ ኒ፡፡ ወ እ መ ሰ፡ ን ቤ ለ ክ ሙ፡ ብ ነ፡ ሱ ታ ፌ፡ ም ስ ሌ ሁ፡ ወ ው ስ ተ፡ ጽ ል መ ት፡ ነ ሐ ው ር፡ ን ሔ ሱ፡ ወ ኢ ን ገ ብ ራ፡ ለ ጽ ድ ቅ፡ ወ ለ ር ት ዕ፡፡ ወ እ መ ሰ፡ ው ስ ተ፡ ብ ር ሃ ን፡ ነ ሐ ው ር፡ በ ከ መ፡ ው እ ቱ፡ ብ ር ሃ ን፡ ሱ ቱ ፋ ን፡ ን ሕ ነ፡ በ በ ይ ና ቲ ነ፡ ወ ደ ሙ፡ ለ ኢ የ ሱ ስ፡ ክ ር ስ ቶ ስ፡ ያ ነ ጽ ሐ ነ፡ እ ም ኵ ሉ፡ ኀ ጣ ው ኢ ነ፡፡ ወ እ መ ሰ፡ ን ብ ል፡ አ ል ብ ነ፡ ኀ ጢ አ ት፡ ን ጌ ጊ፡ ለ ር እ ስ ነ፡ ወ አ ል ቦ፡ ር ት ዕ፡ ኀ ቤ ነ፡፡ ወ እ መ ሰ፡ ነ ገ ር ነ፡ ወ አ መ ነ፡ ኀ ጢ አ ተ ነ፡ ም እ መ ን፡ ው እ ቱ፡ ወ ጻ ድ ቅ፡ ከ መ፡ ይ ኅ ድ ግ፡ ለ ነ፡ ኀ ጣ ው ኢ ነ፡ ወ ያ ነ ጽ ሐ ነ ነ፡ እ ም ኵ ሉ፡ አ በ ሳ ነ፡፡ ወ እ መ ሰ፡ ን ቤ፡ ኢ አ በ ስ ነ፡ ሐ ሳ ዌ፡ ን ሬ ስ ዮ፡ ሎ ቱ፡ ወ ቃ ሉ ኒ፡ ኢ ሀ ሎ፡ ኀ ቤ ነ፡፡

## ፩፥፳፥፪ መልእክተ ዮሐንስ በውርድ እና በቁም ንባብ

መልእክተ ዮሐንስ ሐዋርያ ወልደ ዘብዴዎስ ቀዳማዊ ንዜንወክሙ በእንተ ውእቱ ዘሀሎ እምቅድም ውእቱ ዘሰማዕናሁ በእዘኒነ ወዘርኢናሁ በአዕይንቲነ ወዘጠየቅናሁ ወዘገሠሣሁ እደዊነ በእንተ ነገረ ሕይወት። እስመ ሕይወት ተአውቀት ለነ ወርኢናሃ ወስማዐ ኮነ ወንዜንወክሙ ለክሙኒ ሕይወተ እንተ ለዓለም እንተ ሀለወት ኀበ አብ ወተዐውቀት ለነ። ወርኢናሃ ወሰማዕናሃ ወንዜንወክሙ ለክሙኒ ከመ አንትሙኒ ትኩኑ ሱታፌ ምስሌነ ወሱታፌነሰ ምስለ አብ ወምስለ ወልዱ ኢየሱስ ክርስቶስ። ወዘንተ ንጽሕፍ ለክሙ ከመትፍሥሕትክሙ ፍጽምተ ትኩን ብነ። ወዛቲ ይእቲ ዜና እንተ ሰማዕናሃ ትካት እምኔሁ ወንዜንወክሙ ከመ እግዚአብሔር ብርሃን ውእቱ ወጽልመትሰ አልቦ ኀቤሁ ወኢአሐተኒ። ወእመሰ ንቤለክሙ ብነ ሱታፌ ምስሌሁ ወውስተ ጽልመት ነሐውር ንሔሱ ወኢንገብራ ለጽድቅ ወለርትዕ። ወእመሰ ውስተ ብርሃን ነሐውር በከመ ውእቱ ብርሃን ሱቱፋን ንሕነ በበይናቲነ ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያነጽሐነ እምኵሉ ኀጣውኢነ። ወእመሰ ንብል አልብነ ኀጢአት ንጌጊ ለርእስነ ወአልቦ ርትዕ ኀቤነ። ወእመሰ ነገርነ ወአመነ ኀጢአተነ ምእመን ውእቱ ወጻድቅ ከመ ይኅድግ ለነ ኀጣውኢነ ወያነጽሐነ እምኵሉ አበሳነ። ወእመሰ ንቤ ኢአበስነ ሐሳዌ ንሬስዮ ሎቱ ወቃሉኒ ኢሀሎ ኀቤነ።

# ምዕራፍ ክልኤቱ
# የግእዝ አኃዝ ከ፩ እስከ ፲

## የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

ከ፩ እስከ ፲ ያሉትን የግእዝ ቊጥሮችን በቃልም በጽሑፍም ይጠነቀቃሉ።

## ተስእሎታተ መራኁት (የመክፈቻ ጥያቄዎች)

፩. ኦ አርድእት ተአምርኑ አኃዘ ግእዝ?
፪. ኦ አርድት እስኩ ተናገሩ ለመምህርክሙ እምቅድመዝ ዘተአምሩ አኃዘ ግእዝ?

## ፪. የግእዝ አኃዝ ከ፩ እስከ ፻

### ዘግእዝ አኃዝ እም ፩ እስከ ፲

| የግእዝ ቍጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቍጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቍጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| | አልቦ | 0 | ዜሮ |
| ፩ | አሐዱ | 1 | አንድ |
| ፪ | ክልኤቱ | 2 | ሁለት |
| ፫ | ሠለስቱ | 3 | ሦስት |
| ፬ | አርባዕቱ | 4 | አራት |
| ፭ | ኃምስቱ | 5 | አምስት |
| ፮ | ስድስቱ | 6 | ስድስት |
| ፯ | ሰብዓቱ | 7 | ሰባት |
| ፰ | ሰመንቱ | 8 | ስምንት |
| ፱ | ተስዓቱ | 9 | ዘጠኝ |
| ፲ | ዐሠርቱ | 10 | ዐሥር |

### ዘግእዝ አኃዝ እም፳ እስከ ፻

| የግእዝ ቍጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቍጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቍጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፳ | ዕሥራ | 20 | ሃያ |
| ፴ | ሠላሳ | 30 | ሠላሳ |
| ፵ | አርብዓ | 40 | አርባ |
| ፶ | ኃምሳ | 50 | ኃምሳ |
| ፷ | ስድሳ/ ስሳ | 60 | ስልሳ |
| ፸ | ሰብዓ | 70 | ሰባ |
| ፹ | ሰማንያ | 80 | ሰማንያ |
| ፺ | ተስዓ | 90 | ዘጠና |
| ፻ | ምእት | 100 | መቶ |

## ምልማድ አሐዱ

የሚከተሉትን የግእዝ ቊጥሮች በአኃዝ ጻፉ።

፩. ሠለስቱ ምእት ---------

፪. አርባዕቱ ምእት ----------

፫. ኀምስቱ ምእት ----------

፬. ስድስቱ ምእት ----------

፭. ሰብዓቱ ምእት ----------

## ምልማድ ክልኤቱ

፩. ከአንድ እስከ ዐሥር ያሉትን ቃላት ደጋግማችኹ በቃላችኹ ካላችኹ በኋላ በጽሑፍ ለመምህራችኹ አሳዩ።

______________________________________________________________

______________________________________________________________

፪ ከሚከተሉት አኃዛት ውስጥ ሃያ ቊጥርን ያመለክታል

ሀ. ፴ ለ. ፵ ሐ. ፳ መ. ፺

፫. ከዚህ በታች ያሉትን የግእዝ ቊጥሮች በግእዝ እና በአማርኛ ጻፏቸው

ሀ. ፩ ________________________________

ለ. ፫ ________________________________

ሐ. ፬ ________________________________

መ. ፭ ________________________________

ሠ. ፮ ________________________________

ረ. ፯ ________________________________

ሰ. ፳ ________________________________

ሸ. ፱ ________________________________

ቀ. ፲ ________________________________

ምሳሌ፦ ፩ = አሐዱ = አንድ

፬. ከዚህ በታች ያሉትን የግእዝ ቊጥሮችን በግእዝ ጻፏቸው

ሀ. ፳ ____________________

ለ. ፴ ____________________

ሐ. ፵ ____________________

መ. ፶ ____________________

ሠ. ፷ ____________________

ረ. ፸ ____________________

ሰ. ፹ ____________________

ቀ. ፺ ____________________

በ. ፻ ____________________

ምሳሌ፡-፳ = ዕሥራ

## ዘግእዝ አኃዝ እም ፲–፲፱

| የግእዝ ቊጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቊጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቊጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፲ | ዐሥርቱ | 10 | ዐሥር |
| ፲፩ | ዐሠርቱ ወአሐዱ | 11 | ዐሥራ አንድ |
| ፲፪ | ዐሠርቱ ወክልኤቱ | 12 | ዐሥራ ኹለት |
| ፲፫ | ዐሠርቱ ወሠለስቱ | 13 | ዐሥራ ሦስት |
| ፲፬ | ዐሠርቱ ወአርባዕቱ | 14 | ዐሥራ አራት |
| ፲፭ | ዐሠርቱ ወኃምስቱ | 15 | ዐሥራ አምስት |
| ፲፮ | ዐሠርቱ ወስድስቱ | 16 | ዐሥራ ስድስት |
| ፲፯ | ዐሠርቱ ወሰብዓቱ | 17 | ዐሥራ ሰባት |
| ፲፰ | ዐሠርቱ ወስምንቱ | 18 | ዐሥራ ስምንት |
| ፲፱ | ዐሠርቱ ወተስዓቱ | 19 | ዐሥራ ዘጠኝ |

## የግእዝ አኃዝ ከ፳-፳፱

| የግእዝ ቁጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቁጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቁጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፳ | ዕሥራ | 20 | ሃያ |
| ፳፩ | ዕሥራ ወአሐዱ | 21 | ሃያ አንድ |
| ፳፪ | ዕሥራ ወክልኤቱ | 22 | ሃያ ኹለት |
| ፳፫ | ዕሥራ ወሠለስቱ | 23 | ሃያ ሦስት |
| ፳፬ | ዕሥራ ወአርባዕቱ | 24 | ሃያ አራት |
| ፳፭ | ዕሥራ ወኃምስቱ | 25 | ሃያ አምስት |
| ፳፮ | ዕሥራ ወስድስቱ | 26 | ሃያ ስድስት |
| ፳፯ | ዕሥራ ወሰብዓቱ | 27 | ሃያ ሰባት |
| ፳፰ | ዕሥራ ወስምንቱ | 28 | ሃያ ስምንት |
| ፳፱ | ዕሥራ ወተስዓቱ | 29 | ሃያ ዘጠኝ |

## የግእዝ አኃዝ ከ፴-፴፱

| የግእዝ ቁጥሮች በአኀዝ | የግእዝ ቁጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቁጥር | በአማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፴ | ሠላሳ | 30 | ሠላሳ |
| ፴፩ | ሠላሳ ወአሐዱ | 31 | ሠላሳ አንድ |
| ፴፪ | ሠላሳ ወክልኤቱ | 32 | ሠላሳኹለት |
| ፴፫ | ሠላሳ ወሠለስቱ | 33 | ሠላሳ ሦስት |
| ፴፬ | ሠላሳ ወአርባዕቱ | 34 | ሠላሳ አራት |
| ፴፭ | ሠላሳ ወኃምስቱ | 35 | ሠላሳ አምስት |
| ፴፮ | ሠላሳ ወስድስቱ | 36 | ሠላሳ ስድስት |
| ፴፯ | ሠላሳ ወሰብዓቱ | 37 | ሠላሳ ሰባት |
| ፴፰ | ሠላሳ ወስምንቱ | 38 | ሠላሳ ስምንት |
| ፴፱ | ሠላሳ ወተስዓቱ | 39 | ሠላሳ ዘጠኝ |

## የግእዝ አኃዝ ከ፵-፵፱

| የግእዝ ቁጥሮች በአኀዝ | የግእዝ ቁጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቁጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፵ | አርብዓ | 40 | አርባ |
| ፵፩ | አርብዓ ወአሐዱ | 41 | አርባ አንድ |
| ፵፪ | አርብዓ ወክልኤቱ | 42 | አርባ ኹለት |
| ፵፫ | አርብዓ ወሠለስቱ | 43 | አርባ ሦስት |
| ፵፬ | አርብዓ ወአርባዕቱ | 44 | አርባ አራት |
| ፵፭ | አርብዓ ወኃምስቱ | 45 | አርባ አምስት |
| ፵፮ | አርብዓ ወስድስቱ | 46 | አርባ ስድስት |
| ፵፯ | አርብዓ ወሰብዓቱ | 47 | አርባ ሰባት |
| ፵፰ | አርብዓ ወስምንቱ | 48 | አርባ ስምንት |
| ፵፱ | አርብዓ ወተስዓቱ | 49 | አርባ ዘጠኝ |

## ዘግእዝ አኃዝ እም ፶-፶፱

| የግእዝ ቍጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቍጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቍጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፶ | ኀምሳ | 50 | ኀምሳ |
| ፶፩ | ኀምሳ ወአሐዱ | 51 | ኀምሳ አንድ |
| ፶፪ | ኀምሳ ወክልኤቱ | 52 | ኀምሳ ኹለት |
| ፶፫ | ኀምሳ ወሠለስቱ | 53 | ኀምሳ ሦስት |
| ፶፬ | ኀምሳ ወዐርባዕቱ | 54 | ኀምሳ አራት |
| ፶፭ | ኀምሳ ወኃምስቱ | 55 | ኀምሳ አምስት |
| ፶፭ | ኀምሳ ወስድስቱ | 56 | ኀምሳ ስድስት |
| ፶፯ | ኀምሳ ወሰብዓቱ | 57 | ኀምሳ ሰባት |
| ፶፱ | ኀምሳ ወስምንቱ | 58 | ኀምሳ ስምንት |
| ፶፱ | ኀምሳ ወተስዓቱ | 59 | ኀምሳ ዘጠኝ |

**የግእዝ አኃዝ ከ፷-፷፱**

| የግእዝ ቍጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቍጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቍጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፷ | ስሳ | 60 | ስልሳ |
| ፷፩ | ስሳ ወአሐዱ | 61 | ስልሳ አንድ |
| ፷፪ | ስሳ ወክልኤቱ | 62 | ስልሳ ኹለት |
| ፷፫ | ስሳ ወሠለስቱ | 63 | ስልሳ ሦስት |
| ፷፬ | ስሳ ወአርባዕቱ | 64 | ስልሳ አራት |
| ፷፭ | ስሳ ወኃምስቱ | 65 | ስልሳ አምስት |
| ፷፮ | ስሳ ወስድስቱ | 66 | ስልሳ ስድስት |
| ፷፯ | ስሳ ወሰብዓቱ | 67 | ስልሳ ሰባት |
| ፷፰ | ስሳ ወስምንቱ | 68 | ስልሳ ስምንት |
| ፷፱ | ስሳ ወተስዓቱ | 69 | ስልሳ ዘጠኝ |

**የግእዝ አኃዝ ከ፸-፸፱**

| የግእዝ ቍጥሮች በአኀዝ | የግእዝ ቍጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቍጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፸ | ሰብዓ | 70 | ሰባ |
| ፸፩ | ሰብዓ ወአሐዱ | 71 | ሰባ አንድ |
| ፸፪ | ሰብዓ ወክልኤቱ | 72 | ሰባ ኹለት |
| ፸፫ | ሰብዓ ወሠለስቱ | 73 | ሰባ ሦስት |
| ፸፬ | ሰብዓ ወአርባዕቱ | 74 | ሰባ አራት |
| ፸፭ | ሰብዓ ወኃምስቱ | 75 | ሰባ አምስት |
| ፸፮ | ሰብዓ ወስድስቱ | 76 | ሰባ ስድስት |
| ፸፯ | ሰብዓ ወሰብዓቱ | 77 | ሰባ ሰባት |
| ፸፰ | ሰብዓ ወስምንቱ | 78 | ሰባ ስምንት |
| ፸፱ | ሰብዓ ወተስዓቱ | 79 | ሰባ ዘጠኝ |

## የግእዝ አኃዝ ከ፹-፹፱

| የግእዝ ቍጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቍጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቍጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፹ | ሰማንያ | 80 | ሰማንያ |
| ፹፩ | ሰማንያ ወአሐዱ | 81 | ሰማንያ አንድ |
| ፹፪ | ሰማንያ ወክልኤቱ | 82 | ሰማንያ ኹለት |
| ፹፫ | ሰማንያ ወሠለስቱ | 83 | ሰማንያ ሦስት |
| ፹፬ | ሰማንያ ወአርባዕቱ | 84 | ሰማንያ አራት |
| ፹፭ | ሰማንያ ወኃምስቱ | 85 | ሰማንያ አምስት |
| ፹፮ | ሰማንያ ወስድስቱ | 86 | ሰማንያ ስድስት |
| ፹፯ | ሰማንያ ወሰብዓቱ | 87 | ሰማንያ ሰባት |
| ፹፰ | ሰማንያ ወስምንቱ | 88 | ሰማንያ ስምንት |
| ፹፱ | ሰማንያ ወተስዓቱ | 89 | ሰማንያ ዘጠኝ |

## የግእዝ አኃዝ ከ፺-፺፱

| የግእዝ ቍጥሮች በአኃዝ | የግእዝ ቍጥሮች በፊደል | የዐረብኛ ቍጥር | በዐማርኛ ፊደል |
|---|---|---|---|
| ፺ | ተስዓ | 90 | ዘጠና |
| ፺፩ | ተስዓ ወአሐዱ | 91 | ዘጠና አንድ |
| ፺፪ | ተስዓ ወክልኤቱ | 92 | ዘጠና ኹለት |
| ፺፫ | ተስዓ ወሠለስቱ | 93 | ዘጠና ሦስት |
| ፺፬ | ተስዓ ወአርባዕቱ | 94 | ዘጠና አራት |
| ፺፭ | ተስዓ ወኃምስቱ | 95 | ዘጠና አምስት |
| ፺፮ | ተስዓ ወስድስቱ | 96 | ዘጠና ስድስት |
| ፺፯ | ተስዓ ወሰብዓቱ | 97 | ዘጠና ሰባት |
| ፺፰ | ተስዓ ወስምንቱ | 98 | ዘጠና ስምንት |
| ፺፱ | ተስዓ ወተሰዓቱ | 99 | ዘጠና ዘጠኝ |

## ምልማድ ሠለስቱ

አዛምድ

አስተዛምዱ እለ ተጽሕፉ በውስተ ክፍለ ፊደል ሀ እለ ተጽሕፉ በውስተ ክፍለ ፊደል በ.

| ሀ | | በ |
|---|---|---|
| ፩ | ተስዓ ወተሰዐቱ | አ. ፺ |
| ፪ | ተስዓ | በ. ፳ |
| ፫ | ዕሥራ | ገ. ፺፱ |
| ፬ | ሠላሳ | ደ. ፲፫ |
| ፭ | ዐሠርቱ ወሠለስቱ | ሀ. ፴ |

## ፪፡፪ የቤትና የስልክ ቁጥር (ዘቤት ወምስማዕ ትልቍ)

የስልክ ቁጥር

| ተ.ቁ | የስልክ ቁጥር በግእዝ | የስልክ ቁጥር በአማርኛ |
|---|---|---|
| ፩ | ፱-፲፩-፳-፴፱-፺ | 09-11-20-39-90 |
| ፪ | ፱-፲፪-፳፱-፶፫-፵፪ | 09-12-29-53-42 |
| ፫ | ፱-፲፫-፸፪-፲፱-፸፯ | 09-13-72-19-77 |
| ፬ | ፱-፲፱-፳-፶፭-፺፬ | 09-19-20-55-94 |
| ፭ | ፱—፲፱—፵-፳፭-፷፫ | 09-14-40-25-63 |

የቤት ቁጥር

በአዲስ አበባ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኙ የቤት ቁጥሮች የተወሰኑ ዝርዝሮች

| ተ.ቁ | የቤት ቁጥር በግእዝ | የቤት ቁጥር በአማርኛ |
|---|---|---|
| ፩ | ፭፻፹፮ | 586 |
| ፪ | ፭፻፴፱ | 539 |
| ፫ | ፬፻፶፭ | 455 |
| ፬ | ፱፻፲፱ | 919 |
| ፭ | ፯፻፸፪ | 772 |

## ምልማድ አርባዕቱ

፩. እስኩ ጸሐፉ ዘዚኣክሙ ትልቄ ቤት (የቤት ቁጥራችሁን ጻፉ።)

፪ እስኩ ተናገሩ ወጸሐፉ ዘአቡክሙ ትልቄ ምስማዕ (የአባታችሁን ስልክ ቁጥር ጻፉ።)

፫. እስኩ ተናገሩ ወጸሐፉ ዘእምክሙ ትልቄ ምስማዕ (የእናታችሁን ስልክ ቁጥር ጻፉ።)

# ምዕራፍ ሠለስቱ
# መራሕያን

## የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

ዐሥሩንም መራሕያን ይለያሉ

## ተስእሎታተ መራኁት (የመክፈቻ ጥያቄዎች)

፩. አርድእት እምቅድመዝ ተአምሩኑ ዘይትበሃል መራሕያን
፪. እስፍንቱ ውእቶሙ መራሕያን
፫. እስኩ ተናገሩ እምቅድመዝ ዘተአምሩ መራሕያን

## ፫. መራሕያን

“መርሐ = መራ” ከሚል ግሥ የተገኘ ሁኖ መራሕያን ማለት መሪዎች ማለት ነው። በተለይ በግእዝ ቋንቋ ዋና መሪዎች ፲ ናቸው።

| | | |
|---|---|---|
| ፩ | ውእቱ | እርሱ |
| ፪. | ይእቲ | እርሷ |
| ፫ | ውእቶሙ | እነርሱ(ለወንዶች) |
| ፬. | ውእቶን | እነርሱ(ለሴቶች) |
| ፭. | አንተ | አንተ |
| ፮ | አንቲ | አንቺ |
| ፯ . | አንትሙ | እናንተ(ለወንዶች) |
| ፰ | አንትን | እናንተ(ለሴቶች) |
| ፱. | አነ | እኔ |
| ፲ | ንሕነ | እኛ |

### ፫.፩ በመራሕያን ዓረፍተ መመስረት

ተማሪዎች ከዚህ በታች  የተሰጡትን  ግስ  ለመምህራችኹ በተደጋጋሚ አንብቡላቸው። ካነበባችኹ በኋላ በአምስቱ ግሶች ዓረፍተ ነገር መሥራትን እናያለን።

**ውእቱ**

በልዐ ------› በላ

ሰትየ------› ጠጣ

ሖረ-------› ሔደ

ተዋነየ-------›ተጫወተ

**አነ**

በላዕኩ -------› በላኹ

ሰተይኩ-------› ጠጣኹ

ሖርኩ--------› ሔድኩ

ተዋነይኩ--------›ተጫትኩ

**ንሕነ**

በላዕነ -------› በላን

ሰተይነ------› ጠጣን

ሖርነ-------› ሔድን

ተዋይነ-------›ተጫወትን

**አንተ**

በላዕከ -------› በላኽ

ሰተይከ------› ጠጣኽ

ሖርከ-------› ሔድክ

ተዋነይከ-------›ተጫወትክ

**አንቲ**

በላዕኪ -------› በላሽ

ሰተይኪ------› ጠጣሽ

ሖርኪ-------› ሔድሽ

ተዋነይኪ-------›ተጫወትሽ

**ዓረፍተ ነገር መመሥረት**

በውእቱ

ሀ. ዳዊት በልዐ ኅብስተ

ለ. ያዕቆብ ሰትየ ወይነ

ሐ. ማትያስ ሖረ ኀበ ከኒሳ

መ. ኢሳይያስ ተዋነየ ኵሕለ

## ምልማድ አሐዱ

ምልዑ ርቱዐ አውሥኦተ በውስተ መካነ በድው

አስተዛምዱ ትርጓሜ መራሕያን እለ ተጽሕፉ በውስተ ክፍል ፊደል አ ምስለ ትርጓሜ እለ ተጽሕፉ በውስተ ክፍል ፊደል በ.

| | አ | በ. |
|---|---|---|
| ፩ | አነ | አ. እነርሱ(ለሴቶች) |
| ፪ | ንሕነ | በ. እኛ |
| ፫ | አንተ | ገ. እናንተ(ለወንዶች) |
| ፬ | አንቲ | ደ. አንቺ |
| ፭ | አንትሙ | ገ. እኔ |
| ፮ | አንትን | ሀ. እነርሱ(ለወንዶች) |
| ፯ | ውእቱ | ዘ. እርሱ |
| ፰ | ውእቶን | ሐ. እኔ |
| ፱ | ይእቲ | ጠ. እናንተ(የሴቶች) |
| ፲ | ውእቶሙ | የ. እርሷ |

# ምዕራፍ አርባዕቱ
## አስማተ አዝማድ (የቤተሰብ ስሞች)

### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦
አስማተ አዝማድን ያውቃሉ፣
አስማተ አዝማድን አነ በሚለው መራሕያን ያሳዩበታል።

### ተስእሎታተ መራትት(የመክፈቻ ጥያቄዎች)

፩. አርድእት እምቅድመዝ ተአምሩኑ አስማተ አዝማድ።
፪. በግእዝ እናት እና አባት ምን እንደሚባል ለመምህራችኹ ተናገሩ።

፴ አስማተ አዝማድ (የቤተሰብ ስሞች)

| | |
|---|---|
| አብ | አባት |
| እም | እናት |
| አቡነ | አባታችን |
| እምየ | እናቴ |
| እምነ | እናታችን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| እኅት | እኅት | እኅትየ | እኅቴ |
| እኁ | ወንድም | እኁየ | ወንድሜ |
| ሐው | ወንድ አያት | ሐውየ | አያቴ |
| ሐውት | ሴት አያት | ሐውትየ | አያቴ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዱድ | አኀት | ዱድየ | አኀቲ |
| ዱዲት | አክስት | ዱዲትየ | አክስቲ |
| ቢጽ | ኋደኛ | ቢጽየ | ኋደኛየ |
| ኀር | ኀረቤት | ኀርየ | ኀረቤቲ |

## ምልማድ አሐዱ

አውሥኡ ዘይተልዉ ጥያቄያት( የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ)

፩ መኑ ውእቱ ስመ አቡከ

፪ መኑ ውእቱ ስመ እምከ

## ምልማድ ክልኤቱ

አዛምድ

አስተዛምዱ ትርጓሜ አስማተ አዝማድ እለ ተጽሕፉ በውስተ ክፍል ፊደል ሀ ምስለ ትርጓሜ እለ ተጽሕፉ በውስተ ክፍል ፊደል ለ.

| ሀ | ለ. |
|---|---|
| ፩ አብ | ሀ. አባቴ |
| ፪ እም | ለ. እኅቴ |
| ፫ እኅ | ሐ. ጓደኛ |
| ፬ አቡየ | መ. ወንድም |
| ፭ እምየ | ሠ. እናቴ |
| ፮ እኅት | ረ. እናት |
| ፯ እኁየ | ሰ. እህት |
| ፰ እኅትየ | ሸ. ጓደኛ |
| ፱ ቢጽየ | ቀ. አባት |
| ፲. ቢጽ | በ. ጓደኛየ |

# ምዕራፍ ኃምስቱ

## አስማተ እንስሳ ወዓራዊት አትክልት/ፍራፍሬ ወአዝርዕት

### የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

፩. የተወሰኑ የቤትና የአራዊት እንስሳትን ስም በግእዝ ይለያሉ።


፪. የተወሰኑ የአዝርዕትና የፍራፍሬ ስሞችን በግእዝ ይለያሉ።

### ተስእሎታተ መራኁት(የመክፈቻ ጥያቄዎች)

፩. ዶሮ በግእዝ ምን ተብሎ ይጠራል?

፪. ልጆች ዝሆን በግእዝ ምን ተብሎ ይጠራል?

# አስማተ እንስሳ ወዓራዊት



በግዕ - በግ



ላህም - ላም




ብእራይ - በሬ



ጠሊ- ፍየል



ዶርሆ - ዶሮ



አድግ - አህያ



ፈረስ- ፈረስ



በቅል - በቅሎ



ከልብ - ውሻ



ገመል- ግመል



ሔሤሜት - ድመት



ነጌ - ዝሆን



ብሔ - ጉማሬ



ሲርኖን - ሰጎን



ሀየል - ዋልያ



ሐለስትዮ -ዝንጀሮ



ሔለይ - ዔሊ



ንህብ - ንብ



ነምር - ነብር



ዝእብ - ጂብ



ላጽቂት- እንሽላሊት



ቍንጽል - ቀበሮ

# አስማተ አትክልት/ፍራፍሬ



ስጕርንድ - ሽንኩርት



ሐመል - ጎመን



ተፋሕ - ሙዝ



ከርካዕ - ሎሚ

# አዝርዕት



ስንዳሌ - ስንዴ



ሰገም - ገብስ

# ምዕራፍ ስድስቱ
# ንዋያተ ጽሕፈት

## የትምህርቱ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የጽሕፈት መሳርያዎችን ስም በግእዝ ያውቃሉ


## ተስእሎታተ መራኅት(የመክፈቻ ጥያቄዎች)

፩. ልጆች እርሳስ በግእዝ ምን ተብሎ ይጠራል?

# ንዋያተ ጽሕፈት

## ደብተር - ደብተር



## ምጥሳይ - ላጲስ

## መቅረጽ- መቅረጫ





ሠትር - እርሳስ



ብርዕ - ብዕር